በኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን
የሕዝብ ጉዳይ ጥናት ማዕከል

# የወሊድ ሁኔታና የቤተሰብ ጥናት
# የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ

መጋቢት 1982

<u>አርእስት</u> — <u>ገጽ</u>


<u>የቤተሰብ መጠይቅ</u> 20

የአካባቢ መለያ .......................... 20
የቤተሰብ ዝርዝር ሁኔታ መመዝገቢያ ቅፅ .................. 20
የቤተሰብ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት መጠይቅ .......... 22
የአካባቢ መለያዎች .......................... 22
የቤተሰቡ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት ጥያቄዎች ......... 23

<u>የሴቶች መጠይቅ</u> 25

ክፍል 1 — የአካባቢ መለያዎች ...................... 26
ክፍል 2 — የመልስ ሰጭዎች ባሕርያት .................. 26
ክፍል 3 — የጋብቻ ታሪክ ......................... 31
ክፍል 4 — የልደት ታሪክ ......................... 32
ክፍል 5 — የጤናና የማጥባት ሁኔታ .................. 36
ክፍል 6 — የወሊድ ቁጥጥር ........................ 40
ክፍል 7 — መውለድ የሚፈልጉቸው ልጆች ብዛት ........... 45
ክፍል 8 — የሴቶች የሥራ ሁኔታ፣ የባለቤት ባሕሪያትና የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ልምድ .................... 46

የመረጃ ሰብሳቢ ዕለታዊ የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ 49
ዋና ዋና የታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር .......... 50
አሥር ሺህ እና ከዚያ በላይ ሕዝብ ያላቸው ከተሞች ዝርዝር ......................... 53

ሀ. <u>የቤተሰብ መጠይቅ፤</u> በቤተሰቡ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ አባላትና በቤት ያደሩ እንግዶችን ባሕሪያት በተመለከተ /ዕድሜ፤ ጾታ፤ የጋብቻ ሁኔታ፤... ወዘተ/ ጥያቄዎችን የያዘ ነው::

ለ. <u>የቤተሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት መጠይቅ፤</u> ቤተሰቡን በተመለከተ የተለያዩ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ባሕሪያት የሚያንፀባርቁ ጥያቄዎችን የያዘ ነው::

ሐ. <u>የሴቶች መጠይቅ፤</u> በሰባት ዋና ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን የሚከተለው መረጃ ለመሰብሰብ እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ ነው::

- ስለሴቶች ባሕሪያት /ዕድሜ፤ የትምህርት ሁኔታ፤ ብሔረሰብ፤ ሃይማኖት፤ ...ወዘተ/
- የጋብቻ ሁኔታ /አግብተው ያውቁ እንደሆነ፤ አግብተው የማያውቁ ከሆነ፤ የጋብቻ ዕድሜ፤ የጋብቻ ብዛት፤ ጋብቻው የቆየበት ጊዜ ብዛት፤... ወዘተ/
- ስለልደት ዝርዝር ሁኔታ /የወለዷቸው ልጆች ብዛትና የሞቱባቸው ልጆች ብዛት፤ በእርግዝና ጊዜ ስለ ተከታተሉት የሕክምና ሁኔታ፤...ወዘተ/
- ስለጤናና ጡት ማጥባት /ለምን ያህል ጊዜ ልጆቻቸውን ጡት እንዳጠቡ፤ ስለ ሕጻናት የጸረ ስድስት በሽታ ክትባት ስለማስከተባቸው፤...ወዘተ/
- ስለወሊድ ቁጥጥር /ስለወሊድ ቁጥጥር ያላቸው ዕውቀት፤ አመለካከትና ልምድ/
- መውለድ የሚፈልጉቸው ልጆች ብዛት፤
- የሴቶች የሥራ ሁኔታ፤ የባለቤት ባሕሪያትና የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ልምድ የሚያጠቃልል ነው::

መ. <u>የባሎች መጠይቅ፤</u> የሚከተሉትን መረጃዎች ለመሰብሰብ እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ ነው::

- ዕድሜና የጋብቻ ሁኔታ፤
- የወሊድ ቁጥጥር፤
- ስለማስወረድ ያላቸው አመለካከት፤
- መውለድ የሚፈልጉቸው ልጆች ብዛትና የግብረ ሥጋ ግኑኝነት የሚያጠቃልል ነው::

አቀራረብን ችሎታ ከልምድ ማዳበር የሚቻል ቢሆንም ማንኛውም መረጃ ሰብሳቢ የተሳካ ውጤት ለማስገኘት ሊከተለው የሚገባው መመሪያዎች አሉ:: እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል::

1. <u>ከመልስ ሰጪዎች ጋር መግባባት መፍጠር</u>

መረጃ ሰብሳቢዎና መልስ ሰጪዎች የማይተዋወቁ በመሆናቸው የመረጃ ሰብሳቢዋ ተቀዳሚ ተግባር በሁለት መካከል ጥሩ ዓይነት መግባባትን መፍጠር ነው:: መልስ ሰጪዎች በመጀመሪያ ሲገናኙ በመረጃ ሰብሳቢዋ ላይ ያላት አመለካከትመረጃ ለመስጠት በሚያደርጉት ትብብር ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል:: ስለዚህ መረጃ ሰብሳቢዋ ወደ ቤተሰቡ ቃለ መጠይቅን ለማድረግ በምትሄድበት ወቅት በጥሩ አቀራረብ ሰላምታ በመስጠት እራሷን ማስተዋወቅ ይኖርባታል:: መረጃ ሰብሳቢዎች ለሥራ ከመሠማራታቸው በፊት ተቁጣጣሪው ቤተሰቡ በከተማ ነዋሪዎች ወይም በገበሬ ማህበራት አመራር አባሎች በኩል መረጃ ሰብሳቢ ወደ ቤታቸው እንደምትመጣ እንዲያውቁት ይደረጋል:: ለእያንዳንዷ መረጃ ሰብሳቢም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ሠራተኛ ለመሆኗ መታወቂያ ካርድ ይሰጣል:: ከመልስ ሰጪዎች ጋር መግባባትን ለመፍጠር የሚከተሉትን መመሪያዎች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል::

ሀ. <u>የመጀመሪያ አመለካከታቸው ጥሩ እንዲሆን ማድረግ</u>

መረጃ ሰብሳቢዋ ከግለሰቧ ጋር በምትገናኝበት ወቅት መልስ ሰጪዋ እንዳትጨነቅ ማድረግ ያስፈልጋል:: በፈገግታ ሰላምታ በመስጠት ሊያዝናኑ በሚችሉ ቃላቶች ንግግርን መጀመር ይገባል::

ለምሳሌ ትውውቅን በዚህ ዓይነት መጀመር ይቻላል::

“ስሜ ____________________ ይባላል:: የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ሠራተኛ ነኝ:: ስለ ወሊድ ሁኔታና ስለቤተሰብ በሚመለከት ጥናት እያካሄድን ስለሆነ ለቤቶች ቃለ መጠይቅ እያደረግን ነው:: እርስዎም ለዚህ ጥናት ቃለ መጠይቅ እንዲደረግላቸው ከተመረጡት ቤቶች አንዱ ስለሆኑ ስለዚሁ ጉዳይ አንዳንድ ነገሮች ላነጋግሮትና ልጠይቆት እፈልጋለሁ::”

ለ. <u>ሁል ጊዜ ቀና የሆነ አቀራረብ እንዲኖር</u>

መረጃ ሰብሳቢዋ ቃለ መጠይቅን ለማድረግ ፈቃደኝነት በምትጠይቅበት ወቅት እንቢተኛነትን ሊያስከትል የሚችል ጥያቄ ላለማቅረብ መጠንቀቅ ይኖርባታል:: “ሥራ ይበዛብታል ወይ” “ጥያቄዎችን ለመመለስ ጊዜ ይኖርዎታል ወይ?” ወይም “አንዳንድ ጥያቄዎችን በጠይቆት ቅር ይሉታል ወይ?” የሚሉ ጥያቄዎችን ማቅረብ ፈቃደኝነታቸውን ሊቀንሰው ይችላል:: “አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቆት እፈልጋለሁ” ወይም “ለጥቂት ደቂቃ ላነጋግሮት እፈልጋለሁ” በማለት መጀመሩ የተሻለ ይሆናል::

እነሱም /ሀ/ ኮድ የተሰጣቸው መልሶች ያሏቸው ጥያቄዎችና /ለ/ ከመልስ ሰጪዎች የሚሰጡ መልሶች እንዳለ የሚሞሉላቸው ጥያቄዎች ናቸው::

ሀ. <u>ኮድ የተሰጣቸው መልሶች ያሏቸው ጥያቄዎች መልስ አመዘጋገብ፣</u> ለእነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ከእያንዳንዱ ጥያቄ ቀጥሎ ባለው ቦታ አማራጭ መልሶች ከነኮዳቸው ቀርበዋል:: መልስ ሰጪዎ ለሰጠቸው መልስ ተስማሚ የሆነውን ኮድ በመክበብ መረጃው ይሞላል::

<u>ምሳሌ</u>

| ተራ ቁጥር | ጥያቄ | መልስና ኮድ | ይለፉ |
|---|---|---|---|
| 301 | አግብተው ያውቃሉ ወይም ከወንድ ጋር ኖረው ያውቃሉ? | አዎን .... (1)<br>የለም .... 2 | →324 |

ለጥያቄ 301 መልሱ አዎን ስለሆነ አዎን ለሚለው መልስ የተሰጠው ኮድ "1" በመሆኑ ይኸው ኮድ ይከበባል::

አንዳንድ ጥያቄዎች "ሌላ" የሚል አማራጭ መልስ ያሏቸው አሉ:: የተሰጠው መልስ ከተዘረዘሩት መልሶች ዉጪ ከሆነ "ሌላ" ለሚለው የተሰጠውን መልስ ባለው ክፍት ቦታ በመመዝገብ "ሌላ" ለሚለው የተሰጠውን ኮድ ይከበባል::

<u>ምሳሌ</u>

| ተራ ቁጥር | ጥያቄ | መልስና ኮድ | ይለፉ |
|---|---|---|---|
| 127 | የቤቱ ወለል በአብዛኛው የተሰራው ከምድነው? | ከአፈር ... 1<br>ከሲሚንቶ .. 2<br>ከድንጋይ /ከሸክላ/ 3<br>ከኘላስቲክ ንጣፍ ... 4<br>ከእንጨት .. 5<br>ከሌላ <u>ባጠራ</u> (6)<br>/ይገለጽ/ | |

ለዚህ ጥያቄ የተሰጠው መልስ "ባጠራ" የሚል በመሆኑ ይህም ከተዘረዘሩት ውስጥ ስለሌለ "ከሌላ" ለሚለው አማራጭ መልስ በተሰጠው ቦታ "ባጠራ" ተብሎ ተጽፎ ኮድ "6" ይከበባል::

ከሌለበት ለጥያቄያቸ ከቀረቡ መልሶቸ አጠገብ ወደ ሌላ ጥያቄ መተላለፍ እንደሚገባ የሚገልፁ ትእዛዞቸ ተሰጥተዋል:: ስለዚህ መጠየቅ የሌለባቸው ጥያቄያቸ እንዳይ ቀርቡ እንዚህን ትእዛዞቸ በሚገባ መከተል ያስፈልጋል::

ምሳሌ

| ተራ ቁጥር | ጥያቄ | መልስና ኮድ | ይለፉ |
|---|---|---|---|
| 431 | በአሁኑ ወቀት ነፍሰ ጡር ነሻት? | አዎን ...... 1<br>የለም ...... (2)<br>እርግጠኛ አይደለሁም 8 | <br>→436<br>→436 |

ለ ተሰጠው ጥያቄ የተሞላው ኮድ " 2 " ነው ማለትም ገለሰቧ ነፍሰ ጡር አይደለቸም:: ስለዚህ ጥያቄ 432 – 435 የሚጠየቁው ነፍሰ ጡር ለሆኑ ብቻ ስለሆነ ነፍሰ ጡር ላልሆኑ ሴቶቸ ጥያቄያቸ ይታለፉሉ ማለት ነው::

5. የተሞሉ መጠይ ቁቸን መመርመር

ቃለ መጠይ ቁ እንደ ተጠና ቀቀ መረጃ ሰብሳቢዋ እያንዳንዱን ጥያቄ በማየት መጠይ ቁ በትክክል መሞላ ቱን ማረጋገጥ ይኖርባታል:: መጠየቅ ያለባቸው ጥያቄያቸ አለመዘለላ ቸውንና " ይለፉ " የሚሉ ትእዛዞቸን በሚገባ መከተሏን መመርመር አለባት::

ገልፅ ያልሆኑ መልሶቸ ወይም የማይ ነበቡ ጽሑፎቸን ማስተካከል ያስፈልጋል:: መልስ ሰጪዋን በድጋሚ ማግኘት ቀላል ስለማይሆን ወደ ሌላ ቤተሰብ ከመ ሄድ በፊት እዛው እያሉ መጠይ ቁን በጥንቃቄ በተሰጡት መልሶቸ በመመርመር አስፈላጊውን እርማት ማድረግ የተሻለ ይሆናል::

መረጃው አሞሳል ላይ ገልፅ ያልሆነ ነገር ካለ ማስታወሻ ጥያቄው አጠገብ መጻፍ ተቆጣጣሪውን ማሳከር ያስፈልጋል::

ነገር ግን ወለዱን በወርም በቀንም ከተናገሩ ወለዱ ወይ ቀን ተቀይሮ ይመዘገብላቸዋል:: ወለዱን እያጠጉ ለሚናገሩ ሴቶች ትክክለኛውን ጊዜ እንዲገልጹ መገፋፋት ያስፈልጋል::

ምሳሌ፤

| ወለደ | አመዘጋገብ |
|---|---|
| ሀ. ሦስት ቀናት | 1 \| 0 \| 3 |
| ለ. አሥራ አራት ቀናት | 1 \| 0 \| 2 |
| ሐ. ሰላሳ ቀናት | 1 \| 0 \| 4 |
| መ. ሁለት ሳምንት | 2 \| 0 \| 3 |
| ሠ. አራት ወር | 3 \| 3 \| 3 |
| ረ. ሦስት ዓመት | 4 \| 1 \| 8 |
| ሰ. አንድ ወር ከሦስት ቀናት | 1 \| 1 \| 4 |
| ሸ. አንድ ዓመት ከስድስት ወር | 3 \| 3 \| 0 |
| ቀ. የመጨረሻውን ልጅ ከመገላገላቸው በፊት | 995 |
| በ. የወር አበባ አይተው አያውቁም | 996 |

## ክፍል 5 — የጤናና የማጥባት ሁኔታ

የጤናና የማጥባት ሁኔታዎች በሚመለከት በመጨረሻ ስለተወለደው ልጅና ከርሱ በፊት ስለተወለደው ልጅ ይጠየቃል:: እነዚህ ጥያቄዎች ለሴቶች በሚቀርቡበት ወቅት የልጆችን ስም እየጠሩ መሆን ይኖርበታል::

502. የመጨረሻው ልጅ ስምና ከመጨረሻው በፊት የተወለደው ልጅ ስም የልደት ታሪክ ሠንጠረዥን በመመልከት ይመዘገባል::

503. የመጨረሻውና ከመጨረሻው በፊት የተወለደው ልጅ በልደት ታሪክ ሠንጠረዥ የተመዘገቡበት የመስመር ቁጥር ጥ412 በመመልከት ይመዘገባል::

504. የመጨረሻው ልጅና ከመጨረሻው በፊት የተወለደው ልጅ በሕይወት መኖራቸው ወይም አለመኖራቸው በልደት ታሪክ ሠንጠረዥ ጥ417 በመመልከት በሣጥኑ ውስጥ የ "  " ምልክት በማድረግ ይመዘገባል:: በሕይወት ሳሉ ለሞቱ ልጆች ሁሉ ከጥያቄ 505 — ጥያቄ 519 ያሉት ይጠየቁላቸዋል::

513. ለልጅ ተጨማሪ ምግብ መስጠት የተጀመረው ከተወለደ በስንተኛው ወር እንደነበረ ተጠይቆ ዕድሜው በጨረሰው ሙሉ ወር ይመዘገባል::

517. አንዲት ሴት ልጅ እንደወለደች ወዲያውኑ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት መፈጸም አትጀምር ይሆናል:: ለዚህም ምክንያት ከሚሆኑት ውስጥ፣ ባሕሉ ለተወሰነ ጊዜ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት የሚከለክል በመሆኑ፣ ለሴትየዋ ጤንነት በማሰብ ወይንም ሴትየዋ ልጇን የምትገላገለው ከወላጆቿ ቤት ከሆኑና ከባለቤቷ ጋር በቅርብ ለመገናኘት ያላት ዕድል ያነሰ በመሆኑ፣ እና የመሳሰሉት ምክንያቶች ይገኙበታል:: እነዚህ ምክንያቶች ምንም እንኳን እርግዝናን የሚያራርቁ ቢሆንም ሆነ ብለው እርግዝናን የሚያራርቁ ቢሆንም ሆነ ብለው እርግዝናን ለመቆጣጠር የተፈጸሙ ካልሆኑ በስተቀር እንደ ወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ አይቆጠሩም:: ይህ ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት ሴትየዋ የሚጠየቁት የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ማቋረጣቸውን ብቻ ሳይሆን፣ የግብረ ሥጋ ግኑኝነቱን ያቋረጡት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም እየቻሉ እርግዝናን ለመቆጣጠር ሲሉ መሆኑ መረጋገጥ አለበት::

520. የመጨረሻውና ከመጨረሻው በፊት የተወለደው ልጅ ስም የልደት ታሪክ ሠንጠረዡን በመመልከት ይሞላል::

521. የመጨረሻውና ከመጨረሻው በፊት የተወለደው ልጅ በልደት ታሪክ ሠንጠረዥ የተመዘገቡበት የመስመር ቁጥር ዓምድ 412 በመመልከት ይመዘገባል::

522. የልደት ታሪክ ሠንጠረዥ ዓምድ 417 በመመልከት የመጨረሻው ልጅና ከመጨረሻው በፊት የተወለደው ልጅ በሕይወት መኖራቸው ወይም አለመኖራቸው ይመዘገባል:: የመጨረሻው ልጅ በሕይወት ካለ ከ523 –529 ያሉት ጥያቄዎች ይጠየቁለታል ሆኖም የመጨረሻው ልጅ በሕይወት ከሌለ እነዚህ ጥያቄዎች አይጠየቁለትም:: እንደዚሁም ከመጨረሻው በፊት ለተወለደው ልጅ ከ523 – 529 ያሉት ጥያቄዎች የሚጠየቁለት ልጁ በሕይወት የሚገኝ እንደሆነ ብቻ ነው::

523. ከጥያቄ 523 – 529 በተከታታይ ለመጨረሻው ልጅ ተጠይቀው ከተጠናቀቀ በኋላ እነዚሁ ጥያቄዎች ከመጨረሻው በፊት ለተወለደው ልጅ ይጠየቃሉ:: በዚህ ጥያቄ ልጁ መከተብ አለመከተቡ ሳይሆን የሚጠየቀው የክትባት ካርድ እንዳለው ወይም እንደሌለው ነው:: የክትባት ካርድ አለው ከተባለ ካርዱን እንዲያሳዩ ሴቶቹ ይጠየቃሉ:: ካርዱ ቀርቦ ከታየ ኮድ 1 ሲመዘገብ ካርድ እያለው ካርዱ በመጥፋቱ ወይም ሊገኝ ባለመቻሉ ሊያቀርቡት ካልቻሉ ኮድ 2 ይመዘገብለታል:: ልጁ ተከትቦ ካርድ ግን ያልተሰጠው ወይም ተከትቦ የማያውቅ ከሆነ ኮድ 3 ይመዘገብለታል:: የልጁ የክትባት ካርድ ቀርቦ የታየ ከሆነ ጥያቄ 524 ይሞላለታል:: ነገር ግን የክትባት ካርድ ኖሮት ካርዱን ለማሳየት ሴትየዋ ካልቻሉ ወይም የክትባት ካርድ የሌለው ከሆነ ወደ ጥያቄ 525 ይታለፋል::

825. ቋሚ የሆነ ሥራ የሌላቸው ለምሳሌ፣ የቀን ሙያተኞች ወዘተ. ቋሚ የሆነ ገቢ እንደሌላቸው ይቆጠራሉ:: ቋሚ የሆነ ሥራና የማያቋርጥ ገቢ ያላቸው ለምሳሌ፣ የቢሮ ሠራተኞች፣ ነጋዴዎች፣ ገበሬዎች፣ ወዘተ. ቋሚ የሆነ ገቢ እንዳላቸው ይቆጠራሉ::

827. የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በተመለከተ የሚጠየቁት ጥያቄዎች የሚመለከቱት በአሁኑ ወቅት በጋብቻ ሳይ ላሉ ሴቶች ብቻ ነው:: ይህ ጥያቄ ለአ ለአንዳንድ መልስ ሰጭዎች አሳፋሪ ሊሆን ስለሚችል በተቻለ ያህል አለሰልቦ በማግባባት መቅረብ ይኖርበታል::

829. ለመጨረሻ ጊዜ የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸሙት መቼ እንደነበረ ሴትየዋ በሚሰጡት መልስ መሠረት በቀን ወይም በሳምንት ወይም በወር ወይም በዓመት ይመዘገባል:: መልሱ የሚመዘገበው በአንደኛው አቀጣጠር እንጂ በሁለት መሆን የለበትም:: ምሳሌ፤

| የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸሙበት ጊዜ | ምዝገባ |
|---|---|
| ሀ. ከሦስት ቀናት በፊት | (1) \| 0 \| 3 \| |
| ለ. ከአሥር ቀናት በፊት | (1) \| 1 \| 0 \| |
| ሐ. ከሁለት ሳምንት በፊት | (2) \| 0 \| 2 \| |
| መ. ከሁለት ወራት በፊት | (3) \| 0 \| 2 \| |
| ሠ. ከአንድ ዓመት በፊት | (4) \| 0 \| 2 \| |
| ረ. አንድ ሳምንት ከሁለት ቀናት በፊት | (1) \| 0 \| 9 \| |

## የ1982 የወሊድ ሁኔታና የቤተሰብ ጥናት የመረጃ ሰበባቢዎች
## ዐለታዊ የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ

1. ስበ. አካባቢ/ራስ ገዝ ______
2. አውራጃ ______
3. ገበሬ ማ/ሠፈራ ጣቢያ ______
4. ከተማ ______
5. ከፍተኛ ______
6. ቀበሌ ______

| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | | 12 | | 13 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ቀን | የቤተሰብ ኃላፊ | የምርጫ ተ.ቁ | የቤተሰብ መጠይቅ | | የቤተሰብ ማሕበራዊ ጭና... | | የሴቶች መጠይቅ | |
| | | | | ውጤት/አስተያየት | | ውጤት/አስተያየት | | ውጤት/አስተያየት | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

የውጤት ኮዶች፡

1. መጠይቁ ተጠናቋል
2. አቤት አልተገኘም
3. ተላልፏል
4. በከፊል ተጠናቋል
5. አልተባበረም
6. ቤት ባዶ ሆኗል
7. ቤት ፈርሷል/አልተገኘም
8. ሌላ/ይገለጽ ______

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ቀንና ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ ሚያዝያ 1 1982 ዓ.ም ድረስ ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 43 | ኮሌራ በሽታ የገባበት | 1963 | 19 |
| 44 | የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት | የካቲት 1966 | 16 |
| 45 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከስልጣን የወረዱበት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የተቋቋመበት | መስከረም 2 1967 | 15 |
| 46 | የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በዓል የተከበረበት | ታህሣስ 12 1967 | 15 |
| 47 | የገጠርን መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | የካቲት 25 1967 | 15 |
| 48 | የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | ሐምሌ 19 1967 | 14 |
| 49 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያረፉበት | 1967 | 15 |
| 50 | ብሔራዊ መሠረተ ትምህርት የተጀመረበት | ሰኔ 1971 | 10 |
| 51 | የኢሠፓአኮ አንደኛ ጉባኤ የተካሄደበት | ሰኔ 9 1972 | 9 |
| 52 | በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ብሔራዊ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ተካሄደበት | ግንቦት 1 1976 | 5 |
| 53 | 10ኛ አብዮት በዓል የተከበረበት | መስከረም 2 1977 | 5 |
| 54 | ኢሠፓ የተመሠረተበት | ጳጉሜ 5 1977 | 4 |
| 55 | በሕገ መንግሥት ረቂቅ ላይ ውይይት ተካሄደ | ሰኔ 1978 | 3 |
| 56 | በሕገ መንግሥት ረቂቅ ላይ ድምጽ ተሰጠ | ጥር 24 1979 | 3 |
| 57 | ኢሕድሪ የተመሠረተበት | መስከረም 2 1980 | 2 |

| ተራ ቁጥር | አስተዳደር አካባቢ/ ራስገዝ | አውራጃ | ከተማ | የሕዝብ ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| 66 | ትግራይ | አንደርታ | መቀሌ | 76,400 |
| 67 | " | ራያና አዘቦ | ማይጨው | 17,063 |
| 68 | " | ሽሬ | እንደስላሴ | 15,503 |
| 69 | " | ተንቤን | አቢይ አዲ/ጉያ | 15,745 |
| 70 | ወለጋ | ጊምቢ | ጊምቢ | 17,388 |
| 71 | " | ጉዶ ናዶ | ነቀምቴ | 34,993 |
| 72 | " | ሆሮ ጉዱሩ | ሻምቡ | 10,478 |
| 73 | " | ቄለም | ደንቢ ዶሎ | 17,168 |
| 74 | ሰሜን ወሎ | ራያና ቆቦ | ቆቦ | 15,574 |
| 75 | " | " | አላማጣ | 15,254 |
| 76 | " | ወፍላ | ኩረም | 17,734 |
| 77 | " | የጁ | ወልዲያ | 18,683 |
| 78 | ደቡብ ወሎ | ደሴ ዙሪያ | ደሴ | 87,246 |
| 79 | " | ሰሜን ቃሉ | ኮምቦልቻ | 22,658 |
| 80 | " | " | ባቲ | 12,011 |